# ደንጋራው ብአዴን

በመስከረም አበራ

አምባገነንነት የሃገራችን ገዥዎች መለያ እንደሆነው ሁሉ የእርስበርስ መቋራቆስ ደግሞ የተቃውሞውን ፖለቲካ የተጣባ ክፉ ደዌ ነው፡፡ በተቃውሞ ፖለቲካ ጀማሪዎቹ መኢሶን እና ኢህአፓ መሃከል የነበረው የጎንዮሽ ልፊያ የዚህ አይነተኛ መገለጫ ነው፡፡ በኢህአፓ ውስጠ-ፓርቲ ውስጥ የነበረው እርስበርስ መበላላት ትልቁን ዳቦ (ኢህአፓን) ሊጥ አድርጎት የቀረ አሳዛኝ እውነት ነው፡፡ ይህ ደዌ ኢህአፓን ዝንጀሮ እንዳየው ክምር መበታተኑ ብቻ አይደለም ጥፋቱ-የዘር ፖለቲካን ክፉ ደዌ በህብረ-ብሄራዊ ትግል  እግር ተክቶ ማለፉ እንጅ፡፡

ለዓለማቀፋዊ ላብአደራዊነት ሲታገሉ የኖሩት ኢህአፓ እና መኢሶን በአመዛኙ በራሳቸው የውስጥ ችግር እንዳልሆነ ከሆኑ በኋላ ነበር በዘመኑ እዚህ ግባ የሚባል ፖለቲካዊ ትኩረት ያልነበረው ህወሃት መለምለም የጀመረው፡፡ በሰዓቱ ‘ህብረ-ብሄራዊ ነኝ’ ይል የነበረው ብአዴንም በእናት ፓርቲው ኢህአፓ መቃብር ላይ ነበር ህልውናውን የጀመረው፡፡በጫካ ቆይታው ህብረ-ብሄራዊው ኢህዴን በብሄር ተኮሩ ህወሃት አይዞህ ባይነት ብቻ ሳይሆን ለሎሌነት በተጠጋ ጥገኝነት ስር እንደነበር አቶ ገብሩ አስራት በመፅሃፋቸው በደንብ አብራርተውታል፡፡ ህብረ-ብሄራዊ ነኝ ሲል የታላቋን ሃገር ሁሉንም ህዝብ ፖለቲካዊ ህይወት ለማሻሻል እታገላለሁ ባዩ ኢህዴን ለአንድ ጎሳ እታገላለሁ በሚለው ህወሃት ጉያ ስር ገብቶ ‘አቤት ወዴት’ ማለቱ የአደናጋሪነቱ ጅማሬ ነው፡፡ ከፅንሰት ውልደቱ ጀምሮ ግራ አጋቢነቱ እየባሰበት የሄደው ብአዴን አትኩሮት ሰጥቶ ለሚከታተለው ብዙ አስገራሚም አደናጋሪም ማንነቶችን የተሸከመ ፓርቲ ነው፡፡

ከፖለቲካዊ ፍዘት ወደ ጎሰኝት መኮማተር

ኢህዴን በጫካ ትግሉ ዘመን የትግራይ ነፃ አውጭ ነኝ ባዩ ህወሃት ጋር እጅና ጓንት ሆኖ ወደ አዲስ አበባ ሲገሰግስ የእርሱ ህብረ-ብሄራዊነት ከህወሃት ጎሰኝነት ጋር እንዴት መሰናሰል እንዳለበት ግልፅ አላደረገም፡፡የኢትዮጵያን ህዝብ ወክሎ ሲታገል የትግራይ ህዝብም የኢትዮጵያ ህዝብ ነውና ጥያቄው በኢህዴን ትግል ውስጥ ሊመለስ እንደሚችል ግልፅ ነው፡፡ ነገር ግን ኢህዴን ስሙን የሚመጥን ወታደራዊም ሆነ ፖለቲካዊ ብርታት አልነበረውምና የህብረ-ብሄራዊነትን ታላቅ ስም ይዞም ለአንድ ጎሳ እታገለላለሁ በሚለው ህወሃት እየተዘወረ በሽፍንፍን አዲስ አበባ ገባ፡፡ ኢህአዴግ የሚለው ማዕቀፍ ከተመሰረተ በኋላም በኢህዴንነቱ ቀጠለ፡፡ ኢህአዴግ የሚለው ማዕቀፍም ሆነ በዚህ ስር ገባ የተባለው ኢህዴን ህብረ-ብሄራዊ መሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡ በሽግግር መንግስቱ ወቅትም ኢህዴን በፓርላማ የተወከለው ኢህአዴግ በሚለው ስም ነበር፡፡ በህወሃት፣በሻዕብያ እና በኦነግ ሲዘወር በነበረው የሽግግር ወቅት ፖለቲካ የኢህዴን ሚና ፊዞ ህወሃት ያለውን ‘አዎ አዎ!’ ማለት ነበር፡፡

ኢህዴን ከዚህ ፖለቲካዊ ፍዘት ወደ ባሰው ጎሰኝነት የተኮማተረው በመአድ መመስረት ምክንያት ነበር፡፡ በታዋቂው ሃኪም ፕ/ሮ አስራት ወልደየስ ዋናነት የተመሰረተው መአድ የመመስረቱ ዋነኛ ምክንያት በሽግግሩ ወቅት በአማራ ህዝብ ላይ የወረደው መቅሰፍት ነበር፡፡ ጊዜ ካለፈ በኋላ ህወሃት በኦነግ፣ ኦነግ ደግሞ በህወሃት የሚያላክኩት ግን ከሁለቱ የማይዘል በአማራ ህዝብ ህልውና ላይ የደረሰው ግፍ አንዳች ሃይል የዚህን ህዝብ ድምፅ ለማሰማት መመስረት እንዳለበት ግድ ብሎ ነበር፡፡ ስለሆነም ፕ/ሮ አስራት ግድ ያለ ውድ በአንድ ብሄር ስም ፓርቲ መስርተው የዚህን ህዝብ መከራ ለማቅለል ደፋ ቀና ይሉ ያዙ፡፡በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን መአድ ወደ ህብረብሄራዊነት እንደሚያድግ፣እርሳቸውም ኢትዮጵያዊነታቸውን እንደሚያስቀድሙ ይናገሩ እንደ ነበር መዛግብት ያስረዳሉ፡፡

በመሆኑም የመአድ አባላት አማሮች ብቻ አልነበሩም፡፡ ይልቅስ የሰብዐዊ ፍጡርን እንግልት የማይወድ ሁሉ በመአድ ጥላ ስር ተሰባስቦ በየቦታው ለሚገደለው፣ በገደል ለሚወረወረው አማራ

ጥብቅና መቆም ጀመረ፡፡ይሄኔ ፐ/ሮ አስራት ጥርስ ውስጥ ገቡ፤ ፓርቲያቸውም ሆነ የአባላቶቹ ህልውና አደጋ ውስጥ ገባ፡፡ ይሄኔ የብልጣብልጡ አቶ መለስ ህወሃት መአድን በብአዴን የማጣፋትን ድንቅ ፖለቲካዊ "ጌም" ይዞ ብቅ አለ፡፡ ወትሮም በፖለቲካዊ ፍዘት ውስጥ የነበረው የነታምራት ላይኔ ብአዴን እሳት እንደነካው ላስቲክ ተጨማዶ ብአዴን ለመሆን አላመነታም፡፡ እዚህ ላይ ልብ መባል ያለበት ነገር ለእያንዳንዱ ብሄረሰብ ቆሚያለው የሚለው የኢህአዴግ አባልም ሆነ አጋር ፓርቲ የህወሃትን ቡራኬ ካላገኘ ስንዝር መራመድ አለመቻሉ ነው፡፡ የአማራን ህዝብ ፍዳ ለማስቆም ከልብ ተነሳስቶ የተመሰረተው መአድ አባላት ቤተክርስቲያን እንደገባች ውሻ ሲታደኑ የነበረው አመሰራረታቸው የህወሃት አሻራ ስለሌለበት ነው፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው የሃገሪቱ የሽግግር ዘመን ቻርተርም ሆነ በኋላ ህገ-መንግስቱ ስለመደራጀት መብት የሚያስቀምጡት አንቀፅ ምድር ላይ ነፍስ የሚዘራው ህወሃት ይሁን ብሎ እስትንፋስ ሲዘራበት ብቻ መሆኑን ነው፡፡እውነት እንነጋገር ከተባለ የአማራን ህዝብ ቀልብ በመግዛቱ በኩል ከመአድ እና ከብአዴን የቱ የተሳካለት ነበር/ነው? በትቂቱ ፖለቲካዊ ስሌት ብንሄድ እንኳን መአድ የከሰመው ብአዴን ደግሞ የአማራን ህዝብ እየተሳደበም ቢሆን ሁሌ ተመረጥኩ እያለ የሚያስተዳድረው የአማራን ህዝብ ቀልብ የሚስብ ፖለቲካዊ ማንነት ኖሮት ሳይሆን የባለ ጠብመንጃው ህወሃት የትሮይ ፈረስ ስለሆነ ነው፡፡ የሆነ ሆኖ ብአዴን አንድ የተሳካለት ነገር ቢኖር መአድን አጥፍቶ የህወሃት/ኢህአዴግን ልብ ማረጋጋት መቻሉ ነው፡፡

"ስፊኒክሱ" ፓርቲ

የሃገራችን የብሄር ፖለቲካ ስሪት ከክልሎቹ መጠነ ስፋት ጀምሮ በርካታ አስቂኝ እና ግራ አጋቢ እውነቶች ቢኖሩትም እንደ በአዴን አስቂኝነቱ የሚበረታበት የለም፡፡ ጨቋኝ ሲባል የኖረው አማራ መአድን ለማጥፋት ሲባል ብቻ ከመቅፅበት ተጨቋኝ ሆኖ ብአዴን የሚባል ዲሞክራሲ አማጭ ፓርቲ ተነጎተለት፡፡ ከዚህ ይብስ የሚገርመው ክልሉን እንዲያስተዳድር የተነጎተውን ፓርቲ ከቁንጮው ሆነው የሚያስተዳድሩት ሰዎች የአማራ ክልልን በውል የማያውቁ ውልደት እድገታቸው ከአማራ ክልል የራቀ፣በስነልቦና ሆነ በእምነት ከህዝቡ ጋር የማይዛመዱ ሲሆኑ የፓርቲው የታችኛው መዋቅር ደግሞ ግድ ያለውድ አማሮች እንዲሆኑ ሆነ፡፡ ከላይ በኤርትራዊው በረከት፣ "ኦቦ" በሚባለው የኦሮሞ ጎልማሶች መጠሪያ ማዕረግ የሚታወቀው የጭሮው አዲሱ ለገሰ፣ ከየት እንደሆነ በውል በማይታወቀው ታምራት ላይኔ፣በኮረሙ ካሳ ተ/ብርሃን፣ በአዲስ አበባው ህላዌ ዮሴፍ እና ካሳ ጥንቅሹ፣ የአማራ ህዝብን ሙልጭ አድርጎ በሚሳደበው በደቡቡ ተወላጅ ተፈራ ዋልዋ ሲዘወር የኖረው ብአዴን ከስር ከተፎ አማራ ካድሬዎችን አሰልፎ ሲታይ ከአንገቱ በላይ ሌላ ፍጥረት ከአንገቱ በታች ሰው የሚመስለውን ስፊኒክስ ሃውልት መስሎ ተገትሮ ከመታየት ያለፈ ለማንም ምንም ሲያደርግ አልታየም፡፡

ኢህዴን የኢህአዴግ ምንጭ???

'በጫካ ትግሉ ወቅት ትግራይን የመገንጠል አላማችንን ስህተትነት ወዲያው ተረድተን የመገንጠል ጥያቄችንን ተውን' የሚሉት ህወሃቶች፤ 'ለትግራይ ብቻ ከመታገል ወደ ህብረብሄራዊነት አድገን ኢህአዴግን መመስረታችን ሌላው እርምት የወሰድንበት አቅጣጫ ነው' ባዮች ናቸው፡፡ ኢህአዴግን ከመሰረቱ ትቂት አመት በኋላ ግን ህብረ-ብሄራዊውን ኢህዴን ወደ ብአዴንነት እንዲያንስ ቀጭን ትዕዛዝ ሰጥተው ነበር፡፡ ህወሃቶች ኢህዴንን ወደ ብአዴን ሲያሳንሱ በስመ ኢህአዴግ የሃገሪቱን ፖለቲካ በእናት ፓርቲያቸው ህወሃት በኩል የመዘወሩን ረቂቅ ፖለቲካዊ እቅድ ታሳቢ አድርገው እንደነበረ ፈዛዛው ኢህዴን ይግባው አይግባው የሚያውቀው ራሱ ነው፡፡ የሆነ ሆኖ ህወሃት እንደዚህ ባለ ጥበብ ህወሃትነቱን ሳይለቅ ኢትዮጵያን ለመዘወር ደግሞ ኢህአዴግ የሚለውን ካባ ሲለብስ ደንጋራው ኢህዴን ወደ ጎሰኝነት ተኮማትሮም "እልፍ ሆኛለሁ" እያለ መዘመሩ አልቀረም፡፡

ከሁለት ዓመት በፊት የብአዴንን ይሁን የኢህዴንን 35ኛ አመት በአል ለማክበር በሚደረገው ሽር ጉድ የደኢህዴን እና የኦህዴዶቹ አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ እና አቶ አባ ዱላ ገመዳ በኢቢሲ

ቀርበው ‘የእኛ ፓርቲዎችም የተመዘዙት ከኢህዴን ስለሆነ የኢህዴን ልደት የእኛ ፓርቲዎችም ልደት ነው’ ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ እንደውም አቶ ኃ/ማርያም “የብአዴን 35 አመት ለደኢህዴንም ይሰራል” እንደማለት ሲሉ ነበር፡፡ በየጊዜው የሚያመጡት አዲስ ዜማ የማያልቅባቸው የኢህአዴግ ባለስልጣናት እንደሚያወሩት ከሆነ ኢህዴን ከህወሃት በቀር የሁሉም የኢህአዴግ አባል ፓርቲዎች እናት ፓርቲ ነው ማለት ነው፡፡ይህ ማለት 37ኛ አመቱን “በደሜ በላቤ ደማቅ ታሪክ ፃፍኩ” እያለ ለራሱ እየዘፈነ የሚያከብረው፣ ኢህዴን ይሁን ብአዴን የማይታወቀው ፓርቲ ተሸንሽኖ ኦህዴድ፣ብአዴን እና ደኢህዴንን ሆኗል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ከብአዴን ብቻ ሳይሆን ከደኢህዴንም ከኦህዴድም ስም በፊት ኢህዴን የሚለው ምህፃር መጠቀስ ነበረበት፡፡ በተጨማሪ ከሰሞኑ እየተከበረ ያለው የብአዴን የውልደት በአል ከሆነ ደግሞ በ1985 እንደ መመስረቱ ሰላሳ አምስት አመት የሞላው እንዴት እንደሆነ ለማስረዳት ሚስጥሩን  አቶ ገዱም ሆኑ አቶ ደመቀ የሚያውቁት አይመስለኝም፡፡

ህዝብ አልቦው ብአዴን

በ1968ቱ ማኒፌስቶው “የአማራ ብሄር ጨቋኝ ናት” ሲል በደፈናው አማራን ሁሉ ፈርጆ ከተነሳው ህወሃት ጋር ግንባር ገጥሞ አዲስ አበባ የገባው ኢህዴን ውሎ አድሮ ‘የአማራ ጭቁን ህዝብ ወኪል ነኝ፤ ስሜም “ብአዴን” ነው’ ብሏል፡፡ ለነገሩ ህወሃትም መጠነኛ ስክነት ሲያገኝ ቢያንስ በቃል ሁሉም አማራ ጨቋኝ አይደለም ማለት ጀምሯል፡፡ ሆኖም የትኛው አማራ ነው ጨቋኙ በሚለው ላይ በህወሃት/ኢህአዴግ መንደር ስክነት የለም፡፡ አቶ መለስ ‘ጨቋኙ የሸዋ አማራ ነው’ ሲሉ እነ አቶ በረከት ደግሞ ‘ጨቋኙ የአማራ ገዥ መደብ ነው’ ይላሉ፡፡ለመሆኑ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ታሪክ  ውስጥ ገዥ ሆኖ ያልጨቆነ ዘር ይገኝ ይሆን? አገዛዝ እና ጭቆናስ በሃገራችን ዘር ለይተው የሚገናኙ ጉዳዮች ናቸው? ወይስ ስልጣን ሲያገኝ ጫቋኝ የሚሆነው አማራ ብቻ ነው? አማራ ያልሆኑቱ፣በኢትዮጵያ የገዥነት ስልጣን እርከን ላይ የነበሩ ሰዎች ያስተዳድሩ የነበረው ከጭቆና በራቀ ዲሞክራሲያዊ ዘይቤ ነበር? ይህ ማለት የመጨረሻው ዘውዳዊ አገዛዝ ማገር የነበሩት እነ አቶ ይልማ ደረሳ፣ የደርጉ ባለሟሎች እነ ጓድ ተስፋየ ዲንቃ፣ደበላ ዴንሳ፣ጴጥሮስ ገብሬ፣ተስፋየ ወልደስላሴ፣ፍሰሃ ደስታ ወዘተ አማሮች ባለመሆናቸው ከጨቋኝነቱ ማህበር የሉበትም ማለት ነው! ወይስ እነዚህ ሰዎች በገዥው መደብ ውስጥ ተሰግስገው ያሳዩት የጭቆና ማህበርተኝነት ሃጢያት አማራ ባለመሆናቸው ብቻ ይሰረይላቸውና የጨቋኝነቱን መርገም ሁሉ አማራ ጓዶቻቸው ይወስዳሉ? እንደ ባለአእምሮ ለሚያስብ በጨቋኞች ወንበር የተቀመጠ ቀርቶ ጭቆናን እያየ ያልተቃወመ  ሁሉ የሞራል ፍርደኛ ነው፡፡ በተቀረ ጭቆናን በዘር የሚተላለፍ መርገም አድርጎ አንድን ዘር ማብጠልጠል የበታችነት ከሚያሰቃየው ልቦና የመነጨ ራስን የማስገመት አካሄድ ነው፡፡

እንዲህ ለፍረጃ በቾኮለ ሁኔታ አማራውን ሰድበው ለተሳዳቢ፣ አድነው ለአዳኝ ወጥመድ ሲሰጡ የኖሩት ህወሃት/ኢህአዴጎች ናቸው እንግዲህ ከእለታት አንድ ቀን ኢህዴን ወደ ብአዴን አንሶ ለጭቁኑ አማራ መቆም አለበት ሲሉ ብአዴንን ያነጎቱት፡፡ የብአዴን ለአማራው ህዝብ እውነት መቆም አለመቆም ተጠየቅ ብዙ የሚያከራክረውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ ከዚህ ጋር መነሳት ያለበት ጉዳይ ለብዙ አመታት በተፃፉ መዛግብት ሳይቀር በጨቋኝነት ሲብጠለጠል የኖረው የአማራ ህዝብ እንዴት ነው ነፃ አውጭ ፓርቲ ያስፈለገው? የሚለው ነው፡፡ይህችን ለማለባበስ ነው በአማራው ህዝብ ላይ ብዙ ግፍ ከተሰራ በኋላ(ከአርባጉጉው እና ከበደኖው ዋይታ በኋላ) ህወሃት/ኢህአዴግ የአማራው አርሶ አደር እና የአማራው ገዥ መደብ ተለያይቶ መታየት አለበት እያለ ያለው፡፡ ይህ አባባሉ ቢረጋለትም ህወሃት/ኢህአዴግ ስህተቱን አረመ ብሎ መቀበል ይቻል ነበር፡፡ ግን ይህም አልሰነበተለትም፡፡እንጀራ ፍለጋ ወደ ሃገሩ ሌላ አካባቢ ሰርቶ ለመኖር የሄደውን ደሃ አርሶ አደር “ሞፈር ዘመት” የሚል ስም ተለጥፎለት እንዲፈናቀል ሲደረግ አይተናልና በኢህአዴግ ዘንድ የአማራ ገዥ መደብ ከአማራ አርሶ አደር ተለይቶ ታይቷል ብንባል እንዴት እናምናለን፡፡

ለአማራ ጭቁን አርሶ አደር ብቻ ቆሜያለሁ የሚለው ብአዴን ይህን በተመለከተ አንዳች ነገር ትንፍሽ ያለማለቱ ተልዕኮው ከሚናገረው የአማራህዝብ ጥብቅና ጋር እንደማይገናኝ ያሳብቃል፡፡

ይብስ ብሎ ‘የቆምኩት በአማራ ክልል ላለ አማራ ብቻ ነው’ ሲል እያደር ማነሱን አስመሰከረ፡፡ በህወሃት/ኢ.ህአዴግ አስተሳሰብ ሎተሪ ሊያዞርም ሆነ የጉልበት ስራ ሊሰራ ከክልሉ የወጣ አማራ ሁሉ ነፍጠኛ ነውና ብአዴን ደግሞ የህወሃት/ኢ.ህአዴግ ምልምል ነውና የቆመው በክልሉ ረግቶ ለተቀመጠው አማራ ነው፤ ይህም ትክክል ነው እንበል፡፡ይህን ብለንም ደንጋራው ብአዴን ሌላ ጥያቄ የሚያጭር ነገር ይደቅንብናል፡፡ ‘በባዶ እግሩ የሚሄደው አማራ የትምክህት ልሃጩ ሌሎችን ብሄሮች አብሮ አላኖር አለ’ ሲል በር ዘግቶ የተናገረው ባለስልጣን የሚመራው ፓርቲ ለአማራ ህዝብ ጥቅም ቆሜአድራለሁ ቢል ለመቀበል ማሞ ቂሎን መሆን አለብን፡፡

የብአዴን “የአማራ ብሄርተኝነት”

ባለፈው አመት ይሁን ሁለት አመት የኢ.ህዴን በአል ሰሞን “ኢ.ቢ.ሲ” የብአዴን ባስልጣናት ቀደም ሲል ተናገሩትን ንግግር መልሶ ሲያስደምጥ ሰንብቷል፡፡ እነዚህ ባለስልጣናት ከሚናገሩት ንግግር መካከል ስለ አማራ ብሄርተኝነት የተናገሩት ትክክለኛውን የብአዴን ተልዕኮ አመላካች ነው፡፡ ከአንገትም ሆነ ከአንጀት ለበአዴን አመራሮች አሁን ያለው የአማራ ህዝብ ፈለግ ለሁለት ይከፈላል- የአማራ አርሶ አደር እና የአማራ ልሂቃን በሚል፡፡ የአማራ ልሂቃን የተባሉት በአመዛኙ በኢ.ትዮጵያ አንድነት ስም የሌላውን ብሄር ማንነት የመጨፍለቅ አላማ ያላቸው የቀድሞ ስርዓት ናፋቂ ትምክህተኞች ናቸው ፡፡ የአማራው አርሶ አደር ደግሞ እንደሌሎቹ ብሄሮች ተጨቋኝ ነው፡፡ ስለዚህ የአማራው ብሄርተኝነት ትግል መቃኘት ያለበት በተጨቋኙ አርሶ አደር ነው ባይ ናቸው - ብአዴናዊያኑ፡፡ እዚህ ላይ ብዙ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል፡፡

እንደሚታወቀው የሃገራችን የብሄር ፖለቲካ አጀንዳ የሚቀረፀውም ሆነ የሚዘወረው በየብሄሩ ልሂቃን እንጂ በአርሶ አደሩ አይደለም፡፡ የአማራውን ብሄር ፖለቲካ አጀንዳ ከዚህ ሃቅ የሚለየው ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ የአማራ ልሂቃን የአማራውን ብሄርተኝነት አይቀበሉም የሚለው የብአዴኖች ትንታኔ በሌላ ጎኑ ሲታይ የብአዴን ፖለቲካዊ ማንነት እና የትግል ዘይቤ ለአብዛኞቹ የአማራ ልሂቃን የሚዋጥ አይደለም ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ብአዴን አላማውን የሚያነሱ ተተኪ የአማራ ልሂቃንን በበቂ ሁኔታ ማፍራት አልቻለም ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከጫካ የመጡት የብአዴን ጉምቱዎች ሲያልፉ በእግራቸው ተተክቶ የፓርቲውን ህልውና ቀጣይ የሚያደርግ ተተኪ እንዲቸግር ያደርጋልና የብአዴንን ቀጣይ ህልውና ፈተና ላይ ይጥለዋል፡፡

የብአዴኖች ትንታኔ ሌላው አንጓ የአማራው የብሄርተኝነት ፖለቲካ መቃኘት ያለበት በአርሶ አደሩ ነው የሚለው ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የሃገራችንን የብሄር ፖለቲካ የሚዘውሩትም ሆነ ከፖለቲካው ቱርፋት ትርፍ የሚሰበስቡት የየብሄሩ ልሂቃን እንጂ አርሶ አደሩ አይደለም፡፡ እራሳቸው ብአዴንን የሚዘውሩት አማራነን ባዮቹ የብአዴን ልሂቃንም አርሶ አደሮች አይደሉምና በአባባላቸው መሰረት ሙጥኝ ያሉትን ወንበራቸውን ለአርሶአደሩ መልቀቅ ነበረባቸው፡፡ በተግባር ግን ይህን እንደማያደርጉ ግልፅ ነው፡፡ ስለዚህ የአማራውን ብሄርተኝነት አርሶ አደሩ ይቃኘው ማለት የማይመስል ትርጉም አልባ ነገር ነው፡፡

ከርካሚው ብአዴን

የኢ.ህአዴግ ፖለቲካ ዋና መዘውር የሆነው የብሄር ፖለቲካ ካልተሳኩለት ነገሮች አንዱ የአማራውን ብሄርተኝነት ማምጣት ነው፡፡ ብአዴን በአማራነት ቀረጢ ውስጥ ገብተው ኢ.ትዮጵያዊነታቸውን ሁለተኛ የሚያደርጉ የአማራ ልሂቃንን በሰፊው ማየት ይፈልጋል፡፡ አለቃው ህወሃት የቀድሞው ስርዓት የአማራን ሁለተንተናዊ የበላይነት ለማስፈኑ ከውልደት ፍጥረቱ ጀምሮ የሚያቀነቅነውን ዜማ ለአማራ ህዝብ ቆሜያለሁ የሚለው ብአዴንም የሚያስተጋባው ነው፡፡ይህ ህወሃትን ያደቆነው ሃሳብ ብአዴን ከኢ.ህዴን ወደ ብአዴን እንዲኮማተር የፈለገበት የህወሃት ዋና አላማ ነው፡፡ ህወሃት ስለ አማራ ህዝብ የነበረውን አሁንም የለቀቀው የማይመስለውን አቋም ለመገንዘብ 1968ቱን ማኒፌስቶውን ማንበብ ይጠቅማል፡፡

የአማራውን ብሄር የቀድሞ ስርዓት ብቸኛ ማገር አድርጎ የሚያስበው ህወሃት በቀድሞ ስርዓቶች ለተሰሩ ጥፋቶች ሁሉ አማራው ሃላፊነትን እንዲወስድ ይሻል፡፡ ብአዴንም በዚህ ይስማማል፡፡ አማራው ለአለፈው ጥፋት ሁሉ ሃላፊነት ወስዶ፣ሌሎችን ብሄሮች ቅርታ ጠይቆ ባልሰራው ብቻ ሳይሆን ባልነበረበት ዘመን በተሰራ "ጥፋት" እየተሸማቀቀ እንዲኖር የሚያደርገውን አካሄድም ብአዴን እና ህወሃት የዲሞክራሲያዊ ብሄርተኝነት ድንቅ አብሮ የመኖር ዘይቤ ሲሉ ያሞካሹታል፡፡ ለዚህ ነው አለምነው የአማራ የትምክህት ለሃጭ መራገፍ አለበት ያለው ፣እነ አያሌው ጎበዜ አማራው ከያለበት ሲፈናቀል ጭጭ ያሉት፣ እነ ታምራት ላይኔ የአማራን ህዝብ ሲሳደቡ እና ሲያስገድሉ የኖሩት፡፡

ጠቅለል ሲል የሃገሪቱን ፖለቲካ የሚዘውረው ህወሃት ለረዥም ጊዜ ሲጨቁን ነበር ብሎ የሚያስበውን የአማራ ብሄር ከፍተኛ የስነልቦና የበላይነት የተሸከመ ትምክህተኛ አድርጎ ያስበዋል፡፡ ህወሃት ትምክህት ሲል የሚረዳው በአመዛኙ የአማራውን በአማራ ብሄርተኝነት ቀረጢት ውስጥ ለመግባት ማስቸገርና ለኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት ማድላቱን ነው፡፡ ይህንን ደግሞ በኢትዮጵያዊነት ሽፋን የቀድሞውን የአማራ የላይነት በሃገሪቱ ለማምጣት የአማራ ልሂቃን የሚያደርጉት ጥረት አድርጎ ይተረጉመዋል - ጠርጣራው ህወሃት፡፡ ስለዚህም አማራው ከኢትዮጵያዊነት የስነልቦና ከፍታ ወደ ተጨቋኝ አማራነት ዝቅ እንዲል ይፈልጋል፡፡ ለዚህ ነው ህወሃት በብአዴን አድሮ 'አብዛኛው አማራ እንደሌሎች ብሄረሰቦች በቀድሞው ስርዓት የተጨቆነ ነው' የሚል አዲስ ዘፈን ያመጣው፡፡ ይህ ከአንጀት እንዳልሆነ፣ ህወሃት/ኢህአዴግ አማራን ሁሉ በአንድ የጨቋኝነት አይን እንደሚያይ ጭቁን ነው የሚለውን የአማራ ደሃ አርሶ አደር ከነልጆቹ ያለርህራሄ ሲያፈናቅል አረጋግጧል፡፡ የሆነ ሆኖ ህወሃት/ኢህአዴግ በአዴንን የሚፈልገው አማራው ኢትዮጵያዊነኝ ሚለውን የስነልቦና ከፍታውን(በህወሃት አስተሳሰብ የበላይነት ትምክህቱን) ትቶ ወደ ተጨቋኝ አማራነት የጎሳ ጎሬ እንዲገባለት እንዲሰብክለት ነው፡፡ ይህ ግን እንደታሰበው የሄደ አይመስልም፡፡ መገለጫው ደግሞ ብአዴን  የአማራ ልሂቃንን 'ዲሞክራሲያዊ ብሄርተኝነትን የማይቀበሉ ትምክህተኞች አሉበት' ሲል መውቀሱ ነው፡፡ ይብስ የሚገርመው ብአዴን ውስጥ ያሉ መካከለኛ እና ዝቅተኛ አመራሮች ራሳቸው ለብአዴን አካሄድ ባዳነት ማሳየታቸው ነው፡፡ የአቶ አለምነውን የቅሌተ ንግግር ቀርፀው ለህዝብ ይፋ ያደረጉት በራሱ በበአዴን ዝግ ስብሰባ የተገኙ ካድሬዎቹ መሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡ በተመሳሳይ አቶ በረከት እና አቶ አዲሱ በብአዴን መካከለኛ እና ዝቅተኛ  አመራሮች ላይ ያላቸውን የተመናመነ ተስፋ የተናገሩበት ምሬት የተቀላቀለበት ሚስጥራዊ ንግግር እንድንሰማው ያደረጉት በአዴኖች ናቸው፡፡ ከዚህ የምንረዳው የአማራውን የበረታ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት ወደ ጎሳ ብሄርተኝነት ድንክነት የመከርከም ታላቅ ተልእኮ ያነገበው በአዴን ክርከማው የታሰበውን ያህል እንዳልሰመረለት ነው፡፡